የተሳቀ እንባ

(ፉአድ ሙና)

.

"እማ" ትላለች አፏን በደንብ ያልፈታችው ህፃን ጀርባዋን ሰጥታ ወደ ውጪ እየተመለከተች የቆመችውን እናቷን እያየች። እናቷ ከታላቅ እህቷ ጋር ያወራሉ።

እናትየው ለመውጣት የተዘጋጀች ልጃቸውን እየተመለከቱ መናገር ጀመሩ።

"እና በቃ መውጣትሽ ነው? ምሳሽን ግን በደንብ በልተሻል?"

"ኧረ በደንብ በልቻለሁ። በቃ ልሂድ ደህና ዋይ።"

"ማን ጋ ነው ግን የምትሄጂው?"

"ቤቲን ላገኛት ነው።"

የቤቱን የውጪ በር ከፍታ ወጣች። እናትየው ከኋላቸው "እማ" እያለች የምትነጫነጨው ልጃቸውን ከምንጣፉ ላይ አንስተው አቀፏት።

.

በሩን ዘግታ ከወጣች በኋላ ወደ ፊቷ የተንሸራተተባትን ሻሿን የእጅ ቦርሳዋን ወደ ብብቷ አስገብታ ይዛ አስተካከለች። የወጣትነት የመጀመሪያው የፍካት ድባብ አብቦባታል። የሚያሳሳ የሰውነት ቅርፅ ፣ ሳሙኝ ሳሙኝ የሚል ከንፈር ሌላም ሌላም ብዙ የወጣትነት ፣ የመድረስ ምልክቶች ተንቆጥቁጠውባታል። ሀያት ከህፃንነቷ አንስቶ የምትጠራበት ስም ነው። ሀዩና ፣ ሀዩ ፣ ሀዩዬ እያሉ ያቆላምጧታል። ሀያት መልኳ የቀይ ዳማ ተብሎ የሚገለፅ አይነት ነው። መልኳ የተጋነነ ውበት ባይኖረውም ለክፉ የሚሰጥ አይነት አይደለም። የተጋነነ ውበት ያላቸውን የምንሰይምበት ቃል እንቸገራለን ብለን ባንሰጋ ቆንጆ ናት ልንላት እንችል ነበር። የጠመጠመችው ሻሽ የሀብሀብ የውስጡን ቀለም ይመስላል። በእነርሱ አጠራር "ፒች" የሚባል የቀለም አይነት ያለው ነው። ቀሚሷ ከሻሿ ጋር ተመሳሳይ ቀለም አለው። ከላይ እጇ ሙሉ ሸሚዝ ለብሳለች። ዛሬ ቅዳሜ ነው። እንደ ሀያት ላሉ ከሰኞ እስከ አርብ ያለውን ጊዜ በትምህርት ለሚያሳልፉ ተማሪዎች ውድ እና ተናፋቂ የእረፍት ቀን ነው። ከቤቷ ወጥታ ጥቂት በእግሯ ከተራመደች በኋላ ተክለሀይማኖት አደባባይ ደረሰች። ከተክለሀይማኖት የሜክሲኮ ታክሲ ይዛ ቅዳሜን አብረው ፏ ሊሉ ወደተቀጣጠረቻት ጓደኛዋ ቤቲ ተስፈነጠረች።

.

ቤቲ ከሀያት ቀደም ብላ ሜክሲኮ ከተቀጣጠሩበት ካፌ ተገኝታለች። ዳለቻ ቀለም ያለው ቱታ ሱሪ ፣ በከፊል ገላዋን አሳልፎ የሚያሳይ ስስ ጥቁር ሹራብ ለብሳለች። ከላይ ደግሞ ኮፍያ ደፍታለች። ቤቲ ፈታ ለቀቅ ያለች ልጅ ናት። ደስታን የምታድን አይነት።

ሀያት ከካፌው እንደደረሰች ሰላም ተባብለው ወደ ሞቀ ጨዋታ ገቡ። ሁለቱም የአስራሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። የሚማሩት በከተማዋ ውስጥ ታዋቂ ከሚባሉ የግል ትምህርት ቤቶች በአንዱ ነው። ጨዋታ እየደራ ሰዓቱ እየገፋ ሲመጣ ቤቲ ለሀዩ አንድ ሀሳብ አቀረበች።

"ሀዩ ዛሬ እኮ ከኤርሚ ጋር ቀጠሮ አለን። እሱም ከጀለሱ ጋር ስለሚከሰት አብረን ብንሄድስ?"

"ኧረ አይመሽብኝም?"

"ኧረ የምን መምሸት ነው? አግኝተናቸው ትንሽ ተጨዋውተን ላሽ እንላለን።"
ሀያት በሀሳቡ ተስማማች። ቤቲ ኤርሚያስ ጋር ደውላ ያሉበትን ቦታ ነገረችው። ሰዓቱ ወደ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ተጠግቷል።

.

ቤቲ በርካታ ጊዜ የፍቅር ጓደኛ ይዛለች። መመቻቸት ሲደባበሩ ደግሞ ላሽ መባባል የፍቅቅሮሽ ህይወቷ መመሪያ ነው። ሀዩ ከዚህ ቀደም ረቢቅ የሚባል ፍቅረኛ ነበራት። ከሱ ጋር አብረው እያሉ የአፍላነት እሳታቸው ከንፈር ለከንፈር እስከመነራረስ አዝልቋቸዋል። የቤቲ እንኳ በርካታ ስለሆኑ እና በጉዳዩ ላይም ዘልቃ ስለሄደችበት "ለሷ" ብርቅ የሚባል አይነት አይደለም። ኤርሚ ባለጊዜዋ ነው። ጊዜ ለፍቅረኝነት የመረጠላት። ሙድ ለሙድ ገጥመዋል። ተመቻችተዋል።

.

ኤርሚ የካፌው በር ላይ ሲደርስ ደወለላቸውና ከካፌው ወጡ። የካፌው በር ላይ አንድ ብርማ ኤክስኪዩቲቭ ቆማለች። ኤርሚያስ ከጋቢና ወረደና ቤቲን እና ሀዩን ሰላም ብሏቸው ቤቲን ይዞ ከኋላ ገባ። ሀያት የነገሮች ሂደት በመራት መልኩ ጋቢና ገባች። መኪናውን የያዘው የኤርሚያስ ጓደኛ ነው። ኢስማኢል ይባላል። ነጭ ጂንስ ሱሪ እና ነጭ እጅ ሙሉ ስስ ሹራብ ለብሷል። ከላዩ ላይ እጅ ጉርድ ጃኬት ደርቦበታል። ኤርሚያስ ጂንስ ቁምጣ ለብሷል። ከላይ የደረቱን ቅርፅ አጉልቶ በሚያሳይ ጥቁር እጅ ጉርድ ቲሸርት ተወጣጥሯል።
የመኪናው ሬዲዮ መንዙማ ያጫውታል። ቤቲ የመንዙማውን አንዱን ቃል ይዛ አብራ እያለች ትጨፍራለች። ጭንቅላቷን በድቤው ሪትም ልክ እየወዘወዘች ትቀውጠዋለች። ኤርሚም አብሯት እጁን እያወዛወዘ ይጨፍራል። እስማኢል የስልኩን ካሜራ ከፍቶ ጭፈራቸውን ይቀርፃል። ሀያት እየሳቀች ትመለከታለች።
ኢስማኢል የመኪናው ሬዲዮ ላይ ጣቱን አሳርፎ መንዙማውን አሳለፈው። እንግሊዘኛ ዘፈን ላይ ሆነ። ቤቲ መቀመጫዋን ከወገቧ ጋር በስልት እያሾረች ሁለት እጆቿን ዘርግታ ትደንሳለች። ተሳሳቁ ፣ ፈገጉ። እስማኢል እጆቹን የመኪናው መሪ ላይ እንዳደረገ ሀያትን በአይኑ ሰርቆ አያት። ከዚያም ወደ ኋላ ዞሮ ወደ ኤርሚ ተመለከተ።
"እ ኤርሚ ወዴት ልንዳው?"
"ወደ ሳር ቤት ንዳው፣ ወደ ዶዲ"
መኪናዋ ወደ ሳር ቤት ተወነጨፈች። አራት የዘመኑን እሳቶች ይዛ። ሁለት የደረሱ ፈታኝ ሴትነቶችን አንከብክባ ፣ ከዶዲ ሬስቶራንት በር ላይ ቆመች።

.

ኢስማኢል ከመኪናው ወርዶ አጎንብሶ ወደ ውስጥ ሲመለከት ኤርሚ እና ቤቲ መኪናው ውስጥ መቆየት እንደሚፈልጉና ከሀዩ ጋር መኪናውን እንዲለቁላቸው ጠየቋቸው። ሀያት የመኪናውን በር ከፍታ ወረደች። ያደረገችው ቋቋ ጫማ ነው። ልቧ ከወትሮው በተለየ ይመታል። የኢስማኢል ወንዳወንድነት ገና እንዳየችው ቀልቧን አጥፍቶታል። እየተራመዱ ወደ ሬስቶራንቱ ሲገቡ ጫማዋ ደንቀፍቀፍ አደረጋት። እስማኢል ሊደግፋት በሚመስል መልኩ እጁን ያዛት። የባሰ የልቧ ምት ተዘበራረቀባት። አተነፋፈሷ ተስተጓጎለ። እጁን መያዙን ያልወደደች ለመምሰል ኮስተር ለማለት

ሞከረች። ከንቱ ሙከራ ፣ በልቧ የተፎረሸ ቀሽም ሙከራ። ሬስቶራንቱ ውስጥ ገብተው ወደ ፎቁ ወጥተው ተቀመጡ። ትንሽ እንደቆዩ አስተናጋጅ መጣ። መታዘዝ ባይፈልጉም ለመቀመጥ ሲሉ ሁለቱም ጁስ አዘዙ። የመጀመሪያ ቀን እንደመገናኘታቸው ብዙ ጠለቅ ያለ ወሬ አያወሩም። ስለ ትምህርቷ ፣ ስለ ስራው ብቻ ፤ ወሬው ከዚህ አይዘልም። እስማኢል ከሀያ ሁለት ዓመት አይዘልም። እሷ ደግሞ ገና አስራስምንት አመት አልሞላትም።

"ዎክ ብናደርግስ እዚህ ከምንቀመጥ?" አለ ኢስማኢል።

ትንሽ ተግደረደረችና "እሺ" አለች።

ከመቀመጫቸው ተነስተው ከሬስቶራንቱ ግቢ ወጡ። መኪናው ውስጥ ኤርሚና ቤቲ በስሜት ግለት ታፍነው የስሜታቸውን እሳት በመዳፎቻቸውና በከንፖቻቸው እየተነፈሱት ነው።

ኢስማኢልና ሀያት አስፓልቱን ተሻገሩ። አካባቢው ላይ በክፍት ብረት የታጠረ ግቢ አለ። የሜድሮክ ግቢ ነው። የአጥሩ ዙሪያ የድንጋይ መቀመጫ አለ። ኢስማኢል ተመቻችቶ ተቀመጠ። ቀና ብሎ ሲመለከታት እሷም ተቀመጠች። እንደምንም ራሱን አደፋፍሮ ክንዱን ከአንገቷ ላይ አሳረፈ። አቀፋት። አካባቢው ላይ ሰው አይበዛም። አንዳንድ ሰዎች በመንገዱ ላይ ሲራመዱ ይታያል። ሀያት እና ኢስማኢል አንድ ድንጋይ ላይ ለሁለት ተቀምጠዋል። በመካከላቸው ምንም አይነት ክፍተት የለም። ደግሞ ኢስማኢል ክንዱን ዘርግቶ አቅፏታል። ከሩቅ ለሚያያቸው የቆዩ ፍቅረኞች እንጂ ዛሬ የተገናኙ ፤ ከዚህ ቀደም የማይተዋወቁ አይነት ሰዎች አይመስሉም።

የሀያት ልብ ሰላሙን አጥቷል። ከኢስማኢል ደረት የሚፈልቀው የሽቶው ጠረን ፣ ልቧ የቀለጠለት ወንዳወንድ የሰውነት ቅርጹ ፣ የሚያምረው የፊቱ ገፅታ ፣ ምናልባትም ኤክስኪዩቲቭ መኪናውም ትንሽ ገፅታውን ሳያጎላው አይቀርም ፤ እነዚህ ሁሉ ተደማምረው እጅ አሰጥተዋታል። አሁንም እንዳቀፋት ናት ፤ እየተንሾካሾኩ ፣ ብዙም ውበት በሌለው ድምጿ ፣ በጎረነነ ድምፁ እየተግባቡ። ሀያት እራሷን መቆጣጠር ከበዳት። ብዙዎቹ ሴቶች በፍፁም ደፍረው የማያደርጉትን ነገር ለማድረግ አሰበች። ልትጎርሰው ፣ ከንፈሩ ላይ ልትለጠፍ። "ደግሞ ቢንቀኝስ?" ብላ ተጨነቀች። "የለመደች ባለጌ ናት ብሎ ቢያስበኝስ?" ብላ ተብሰለሰለች። ግን የኢስማኢል ወንዳወንድነት ፣ የልቧ እጅ መስጠት ፣ ስሜቷን የመግታት አቅም አለመኖር ተደራረቡና ሀፍረቷን ገፈፉት። ካቀፋት ክንዱ ወደ ቀኝ ዞረች። እጁን ወደ አንገቱ ወስዳ ከፊቷ አቀረበችው። ከንፈሩን ጎረሰችው። ኢስማኢል አንገቷ ላይ የነበረው እጁ ወደ ታች ወርዶ ወገቧን ይዟል። "እሷ ከጀመረችልኝማ ምን ገዶኝ" የሚል ይመስላል። በደንብ ይስማታል ፣ በደንብ ትስመዋለች።

መንገዱ ላይ ውር ውር የሚሉት ሰዎች ከአስፓልቱ ዳር ተቀምጠው የሚሳሳሙትን እነኢስማኢልን ከመጤፍ አልቆጠሯቸውም። ተዉ ያላቸው የለም። የገላመጣቸው እንኳ አልነበረም። ሰዉ "ጊዜያቸው ነው" እያለ ትቷቸው ይነጉዳል። አሁን አንዱን መንገደኛ አስቁመን አስፓልቱ ጥግ ላይ የሚሳሳሙትን እነኢስማኤልን እያሳየን "ከተገናኙ ሁለት ሰዓት እንኳ በቅጡ አልሞላቸውም።" ብንለው ያምነናል? አይመስሉማ! አይመስሉም። ግን ስሜታቸው ስለ ምክንያታዊነት እና ስለ ድርጊታቸው ውጤት ለማሰብ ጊዜ አልሰጣቸውም። ብቻ ይሳሳማሉ።

.

ተሳስመው ሲረግቡ ፣ እግሮቻቸው መሀል እንደረጠቡ ፣ ቅድም በመካከላቸው የነበረው ሀፍረት ተገፎ

፣ እየተሳሳቁ እጅ ለእጅ ተያይዘው እየተላፉ ሬስቶራንቱ በር ላይ ወደ ቆመው የኢስማኢል መኪና ሄዱ። ቤቲ እና ኤርሚያስ የከንፈር ጨዋታቸውን ጨርሰው ነበር። ኢስማኢል እና ሀያት ወደ መኪናው ገብተው ቅድም በተቀመጡበት መልኩ ተቀመጡ። ሀዩ ጋቢና እንደተቀመጠች ወደ ኋላ ዞራ ቤቲን አየቻትና ሳቀች።

ቤቲ ሳቀችና "ኧረ ሀዩ ሊፒስቲኩስ? ተመቻቻቹ አይደል?"

ሀያት እና ኢስማኢል ተያይተው ተሳሳቁ። ኢስማኢል መኪናውን አስነስቶ መንዳት ጀመረ። ሰዓቱ ወደ አንድ ሰዓት ለመሆን እየተቃረበ ነው። መኪናቸው ካርል አደባባይ ጋ ሲደርስ በመከላከያ የጀርባ አጥር እየታከከ ውስጥ ለውስጥ ሄዶ ሞቢል ጋር ወጣ። ሀሳባቸው ቤቲ ሰፈሯ አለምባንክ ስለሆነ እስከ ጦርሀይሎች ሊሸኟት ነው። ጦርሀይሎች ሲደርሱ ቤቲን አሰናብተው ሀያትን ሰፈሯ ለማድረስ ወደ ተክለሀይማኖት ነዱት። ኤርሚያስ ከኋላ ተቀምጦ በመኪናው ቴፕ ከተከፈተው ዘፈን ጋር አብሮ ጭንቅላቱን በስልት ያነቃንቃል። ተክለሀይማኖት ሲደርሱ ኢስማኢል ስልክ ቁጥሯን ተቀበላት። የሱንም ሰጣት። ልትወርድ ስትል ኤርሚያስ እየሳቀ "ይኸው አይኔን ጨፍኜያለሁ አላያችሁም" አለ። ኢስማኢል ከንፈሯን ስሞ ተሰናበታት።

.

ሀያት ከመኪናው ወርዳ ወደ ሰፈሯ የሚያስገባውን መንገድ እየተራመደች ከቦርሳዋ ውስጥ ቻፒስቲክ አውጥታ ከንፈሯን ተቀባች። ስትወጣ በነበረበት ሁኔታ እናቷ እንድታያት በማሰብ ራሷን ስትወጣ በነበረችበት ሁኔታ ላይ ለመመለስ ሞከረች። ሁሉም ነገር ተዓምር ሆኖባታል። "እንዴት ባብድለት ነው?" ትላለች ራሷን እየታዘበች። ከሰዓታት በፊት ያደረገችው ሁሉ እየገረማት።

ቤት ስትገባ እናቷ ስመው ተቀበሏት። ታናሽ እህቷን አቅፋ ጣቷን እያጮኸች እያጫወተች ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች። ሀያት ለእናቷ የአይኗ ስስት ናት። ለሷ ዛሬም እንቦቀቅላ ናት። ለሷ ምንም የማታውቅ ጨዋ ናት። ልጃቸው ከንፈሯ ዛሬ ሁለት ሰዓት እንኳ አብራው ባልቆየችው ሰው እንደተሳመ ቢነገራት ምናልባት ምድር ላይ በህይወት መኖሯን አምርራ በጠላች ነበር። እናት ናት፣ እናት ፣ ለልጇ ትልቅ ወግ ማዕረግ የምትመኝ እናት።

.

ሀያት መኝታ ክፍሏ ተቀምጣ ስልኳን እያየች በማመንታት ስሜት ውስጥ ትዋልላለች። ደፈረችና ደወለችለት።

"ሄሎ ኢስማኢል"

"ወዬ ማር"

"ቤት ደረስክ?"

"አልደረስኩም ፣ እየነዳሁ ነው ቤት ስገባ እደውልልሻለሁ"

"እሺ ችግር የለውም"

ሀያት ልቧ ኢስማኢልን አምልኮታል። ለመጀመሪያ ጊዜ ሳመችው ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ደወለችለት። መውደዷን የሴትነት ሀፍረቷ እንዲከልልላት አልፈቀደችለትም።

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሞልቶ ጥቂት ደቂቃዎች እንደተቆጠሩ ኢስማኢል ደወለ። ሀዩ ህፃኗን ወደ ሳሎን ወስዳ ለእናቷ ካስረከበች በኋላ መኝታ ክፍሏን ቆልፋ ስልኩን አነሳችው።

"ሀዩዬ ወድጀሻለሁ"
"እኔም ደስ ብለኸኛል"
"ምኔን ወደድሽው ግን?"
"አለ አይደል ሁሉ ነገርህ ደስ ይላል"
እንግዲህ መዋደዳቸውን የተገላለፁት ከተገናኙ አራት ሰዓት ሳይሞላቸው ነው። በስልክ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ማውራት የጀመሩ ንጋት አስራአንድ ሰዓት ድረስ አላቋረጡም። እንቅልፍ የለ ፣ ካርዱ አያልቅ ፣ የባጡን የቆጡን እያወረዱ ሲነጋገሩ ሰዓቱ ነጎደ። ሁለቱም ስለደካከሙ ስሜት ባለዘባቸው ቃላት ተሰነባብተው ስልኩ ተዘጋ። ለዘጠኝ ሰዓታት ያለማቋረጥ ስልክ ማውራት ምናልባት እብደት ሊመስል ይችላል። በሰዓቱ እነርሱ ግን አንድ ሰዓት ታክልም ያወሩ አልመሰላቸውም።
.
የሀያት አባት በጣም ሀይለኛ ናቸው። ሀያት ውጪ ማምሸት የምትፈራበት ዋናው ምክንያትም የአባቷን ቁጣ ፍራቻ ነው።
ሀያት ከእንቅልፏ ስትባንን ፀሀይ ትንሽ ወደ ምዕራብ ተዘንብላ ነበር። እኩለ ቀን አልፎ ስምንት ሰዓት ሆኗል። ስልኳን ስትመለከት ሁለት ሚስድኮል አላት። ኢስማኢል ነበር። ደወለችለት።
"ሀሎ ኢስሚ"
"የኔ ፍቅር ተነሳሽ?"
"አዎ አሁን ተነሳሁ"
"እኔ አሁን ስራ ገብቻለሁ። በቃ ማታ እንገናኛለን።"
ሰፈሯ መጥቶ ሊያገኛት ተስማሙ። ኢስማኢል የአባቱ ድርጅት ውስጥ ነው የሚሰራው። ለቤተሰቡ ደግሞ የመጀመሪያ ልጅ ነው። ሀያት ፈገግታው አይኗ ላይ ውል እያለባት ፍዝዝ ትላለች። በሀያ አራት ሰዓት ውስጥ ብዙ ነገሯ ቅይርይር ብሏል። አስራ ሁለት ሰዓት ገደማ ሲደርስ ኢስማኢል ሰፈር መጥቶ አገኛት። ትንሽ አውርተው በብዛት ተሳስመው ተለያዩ።
ወደ ቤት ስትመለስ ልቧ የሚሰማውን የፍቅር ስሜት ወረቀት ላይ ልትዘረግፈው ግጥም መፃፍ ጀመረች። ብዙ ሰዎች የፍቅር ስሜት ሲሰማቸው አሊያም ልባቸው ሲሰበር ግጥም መፃፍ ይቀናቸዋል። ግጥሙን ፅፋ ስትጨርስ የወረቀቱ ዙሪያ ላይ በቀይ እስክሪፕቶ ትናንሽ ልብ ቅርጾች ሳለች። ግጥሙን ለራሷ ጮክ ብላ አነበበችው።
"ለትንግርት የሳለህ ፣ ወንድነት ነህ ለኔ፣
አንተ በቅተኸኛል ፣ ሌላ ወንድ ለምኔ?
ንገስ ይገባሀል ፣ ዙፋንህ ነው ልቤ፣
ያሻህን እዘዘኝ ፣ አጎነብሳለሁ ከፊትህ ቀርቤ።
የኔ ህልም አንተ ነህ ፣ ምርኮህ መሆን ክብሬ፣
ያሳየኝ ነገዬን ፣ በፈካ ጨረቃ ፣ ካንተው ተሞሽሬ።
ወንድነት ነህ አንተ፣ ሚዛን የለም ሌላ፣
ተፈጥሮ ያላቀችህ ፣ ትለካለህ እንጂ አትልለካም ብላ።"
ግጥሙን አንብባ ስትጨርስ ወረቀቱን ወደ ደረቷ ወስዳ እቅፍ አደረገችው።

.
ዛሬ ሰኞ ነው። ሀዩ የትምህርት ቤቷ ግቢ ውስጥ ከቤቲ እና ሳሚያ ከምትባል ጓደኛዋ ጋር ተቀምጠው ያወራሉ። ሀያት ከኢስማኢል ጋር የደረሱበትን ሁኔታ በተመለከተ አጠር ያለ ሪፖርት አቀረበች። ተደውሎ ወደ መማሪያ ክፍል ከገቡ በኋላ ሀያት መምህሩ የሚያስተምረውን ማዳመጥ ትታ ስለ ኢስማኢል ታስባለች። ፈገግታው እና ወንዳወንድነቱ አይኗ ላይ ድቅን ይላል።
ከከሰዓት ወደ ቤት ለመሄድ ከትምህርት ቤቷ ግቢ ስትወጣ ኢስማኢል የትምህርት ቤታቸው በር ፊትለፊት መኪናውን አቁሞ እየጠበቃት ነበር። ትናንት የተገናኙ አይመስሉም። አመት እንደተነፋፈቁ ተቃቅፈው ሰላም ተባባሉ። መኪናው ውስጥ ገብታ ቦርሳዋን ኋላ ወንበር ላይ አስቀመጠች። ኢስማኢል ወደ ሳር ቤት መኪናውን ነዳው። መኪናው ውስጥ የጥላሁን ገሰሰ ዘፈን ተከፍቷል። ኢስማኢል ፊቱን ወደ ሀያት አዙሮ ከጥላሁን እኩል አብሮ እየጮኸ ያንጎራጉርላት ጀመረ።
"ፍቅርሽ ነው የጎዳኝ ፣ ፍቅርሽ ነው የጎዳኝ ፣ ፍቅርሽ ነው የጎዳኝ!
በልቼ እንዳልበላሁ ፣ ጠጥቼ እንዳልጠጣሁ ፣
ያረገኝ ፍቅርሽ ነው ፣ መች አጣሁ መች አጣሁ።
ከሰው ተራ አውጥቶ ያረገኝ ብቸኛ ፣ አውቃለሁ ፍቅርሽ ነው ፣ ይሄ መዘዘኛ ፣ ይሄ መዘዘኛ።
ነጭናጫ ያረገኝ ፣ ተቆጪ በቶሎ፣
ያው ያንቺው ፍቅር ነው ፣ ሌላ ማን ተብሎ ፣ሌላ ማን ተብሎ?" እያለ አይን አይኗን እያየ እያንጎራጎረላት በየመሀሉ እጇን ጭምቅ አድርጎ እየያዛት ሳር ቤት ደረሱ። ከሩሚ በርገር በር ላይ መኪናቸውን አቁመው ወደ ውስጥ ዘለቁ። ሀዩ አይኑ ላይ ፍዝዝ እንዳለች እሱም ከእቅፉ ሸጉጧት ከከንፈራቸው ፉት እየተባባሉ ያዘዙትን በርገር ይጠብቃሉ። ዛሬ ሀያት እና ኢስማኢል ከተዋወቁ ሶስተኛ ቀናቸው ነው። በመካከላቸው መተፋፈር የለም። በፍፁም ሶስት ቀን ብቻ ያሳለፉ ጥንዶች አይመስሉም። ለእነርሱ ቀናት በሙሉ መፋቀሪያ ፣ ምሽት ሁሉ መነፋፈቂያ ሆኗል። ተመቻችተዋል።
.
ኢስማኢል ሳምንቱን ሙሉ ሀያት ከትምህርት ስትወጣ እየጠበቀ አጫውቶ ወደ ቤቷ ይሸኛታል። ቀናት ቆጥረው የተገናኙበትን ሳምንት አብረው በመዋል ሊያሳልፉት ተቃጠሩ። ገና በጠዋቱ ሊገናኙ ፣ ቀናቸውን ሊሰጣጡ ተስማሙ።
ሀያት ቤተሰቦቿን ጓደኞቿ ጋር እንደምትውል ነግራ ማሳመን ነበረባት። እናቷ የሚወዷትን ልጃቸውን "መልካም ቀን" ብለው ስመው ተሰናበቷት። ከጓደኞቿ ጋር ትጫወት ብለው ፣ ስመው ሸኟት። እርሳቸው ልጃቸው ከወንድ ጋር ለመዋል ብላ ትዋሸኛለች ብለው አያስቡም። ለሳቸው ልጃቸው ጨዋ ናት። ደግሞ በዛ ላይ የአባቷ ቁጣም በደንብ እንደገራት ያስባሉ። ግን ልጅ እናቷ እንዳሰቡት ከቤቲ እና ከሳሚያ ጋር ለመዋል አልነበረም የወጣችው። ይልቁንስ ወድጇዋለሁ ካለችው ሰው ጋር ጊዜዋን ልታሳልፍ ነው።
.
ኢስማኢል መኪናውን እያሽከረከረ ወደ ሱሉልታ ሄዱ። ሱሉልታ ያያ ቪሌጅ ሲደርሱ የምሳ ሰዓት ደርሶ ነበር። መኪናቸውን የመናፈሻው መኪና ማቆሚያ ውስጥ አቁመው ወደ ውስጥ ገቡ። ቦታው በጣም ውብ ነው። መናፈሻው ውስጥ ያለ የሳር ቤት ውስጥ ተቀመጡና ምሳቸውን በሉ። ከዚያም መሟዘዝ ጀመሩ። ልጅ ልጅ መሆን። መጃጃል። ፍቅር የሚባለው ስሜት ትንሽ ከምክንያታዊነት አውጥቶ

ለደቂቃዎች አነስተኛ እብደት ውስጥ ይከታል መሰል። ምሳ ከበሉበት የሳር ጎጆ ወጥተው ሳሩ ላይ ተቀመጡ። ቦታው ደስ የሚል አየር አለው። ኢስማኢል ሁለት እግሩን ወደ ፊትለፊቱ ዘርግቶ ተቀመጠ። ሀዩ ከኢስማኢል እግሮች መካከል እግሯን እሱ በዘረጋበት አቅጣጫ ዘርግታ፤ ወገቧን ደረቱ ላይ አስደግፋ ተቀመጠች። አንገቷን ወደ ኋላ አስተኝታ አይን አይኑን ታየዋለች። ሳማት ፣ በደንብ ሳማት። እግሮቿን ሰብስባ ወደ ደረቱ በደንብ ተጠጋች። አንገቱን ይዛ ትስመዋለች። በዚህ ሰዓት ምድር ላይ ከነሱ ወዲያ ሰው ያለም አይመስላቸውም። ሲሳሳሙ ፣ ሲላላሱ ፣ ከምክንያታዊነት አለም ወጡ። ኢስማኢል እየሳማት በስሜት ሳግ የታፈነ ንግግር ያሰማል።
"እንተኛ? እ? ልሞትብሽ እኮ ነው። እ ሀዩዬ? ላህ ሀዩ ሞትኩ እኮ፣ ቆንጂት እንተኛ የኔ ማር"
ሀያት ያለችበት የስሜት ንዳድ ውስጥ ሆና የስሜት ሲቃው ያስረገዘውን ንግግሩን ታደምጣለች። ከዚህ በፊት ከወንድ ጋር ተኝታ አታውቅም። በፍፁም። ጥያቄውን ችላ ልትለው ሞከረች። ኢስማኢል ግን ከልመና የሚበገር አልሆነም።
"የኔ ውድ ትወጂኝ የለ? ማሬ ልሞትብሽ ነው እኮ ፣ እሺ በይኝ እንተኛ"
ሀያት በእንቢታዋ ለመፅናት ብትሞክርም ኢስማኢልን ማሸነፍ አልቻለችም። ገና ከመጀመሪያ እይታዋ ጀምራ ራሷን አሳልፋ ሰጥታዋለች። ዛሬ ምላሷ እንቢ ቢለውም ልቧ ሊያስከፋው አልፈለገም። "ደሞ ብደብረውስ?" የሚል ስጋት ተፈታትኗታል።
አንገቱ ስር እንደተወሸቀች "እሺ በቃ" አለችው አንገቷ ስር የሚያላዝነውን ኢስማኢልን። እንዲያ ያለ ኩሩ ወንድ እንዲህ አንገቷ ስር ሲያላዝን በጣም ይቀፋል። እሱ ራሱ ተቀርጾ ቢያየው የሚቀፈው ይመስለኛል። ግን ስሜት የጥም እንጂ የምክንያታዊነት ጉዳይ አይደለም። ትንሽ ከስሜታቸው ቀዝቀዝ ለማለት ሞከሩና ተነስተው መኪናቸውን ወዳቆሙበት ቦታ ሄዱ። መኪናው ውስጥ ሲገቡ ኢስማኢል ከመኪናው ቴፕ የሚካኤል በላይነህን ሙዚቃ ከፈተ። ከዘፋኙ እኩል እየጮኸ ፣ እጆቿን በእጁ እየጨመቀ ከያያ ቪሌጅ አቅራቢያ ያለ አንድ ሆቴል በር ላይ ቆመ። ሆቴሉ ባለ አራት ኮከብ ሆቴል ነው። ወግ ላለው ጫጉላ መልካም ቦታ ይመስላል። ኢስማኢል ቀድሟት ከመኪናው ወርዶ ወደ ሆቴሉ የእንግዳ መቀበያ ገባ። ተከተለችው። የክፍሉን ቁልፍ እጁ ላይ እንደያዘ ወደ ፎቅ ወጣ። ሀያት እየተከተለችው ነው። ልቧ በፍርሀት ይርዳል። "አሁን አባዬ ቢሰማ ምን ይል ይሆን?" እያለች ታስባለች። ግን ከአባቷ ንዴት ይልቅ የኢስማኢል ኩርፊያ አስግቷታል። ተከተለችው። የክፍሉን በር ከፍቶ እንድትገባ አስቀደማት። ገባች። ክፍሉ በጣም ያምራል። አልጋው በነጭ አልጋ ልብስ ተሸፍኗል። ከአልጋው አለፍ ብሎ ሁለት ሶፋ ወንበሮች አሉ። የክፍሉ መስኮት የውጪውን ገፅታ በደንብ ያስቃኛል።

.

ኢስማኢል የሀያትን እጅ ጥብቅ አድርጎ ይዞ ወደ ደረቱ አስጠጋት። ከአልጋው እግርጌ አጠገብ ቆመዋል። ከንፈሩን ወደ ከንፈሯ አስጠግቶ ሳማት ፣ ሳማት ፣ ነከሳት።
ብዙውን ጊዜ የህይወታችን መስመር የሚቀየርበትን ጊዜ አናውቅም። ማፍቀር ተብሎ የሚዘመርለትን ጉዳይ አብጠርጥረን በምክንያታዊ አይን መመልከት ይሳነናል። ሀያት ከአባቷ ቁጥጥር እና ከእናቷ ስስት አንፃር ሲታይ እንደዚህ ከወንድ ጋር መኝታ ቤት ውስጥ ትቆማለች ተብሎ አይታሰብ ይሆናል። ግን እንቢ ማለት በቁጥጥር እና በመንሰፍሰፍ ብቻ ሊመጣ የሚችል ጥበብ አይደለም። ግልፅነት የተሞላበት ውይይት ያስፈልገዋል። ጠንካራ የራስ መተማመን መገንባትን ይጠይቃል።

.
ሀያት እና ኢስማኢል ከአልጋው እግርጌ ቆመው ይሳሳማሉ። ይነካከሳሉ። አሁን ኢስማኢል የሀያትን ልብስ ማውለቅ ጀምሯል።

.
ኢስማኢል እጁን ወደ ሀያት ቀሚስ ሰዶ ከሰውነቷ አወረደው። የክፍሉ መብራት ቦግ ብሎ በርቷል። የአምፖሉ ማቀፊያ ከሆቴሉ ግርማ ሞገስ ጋር የገጠመ ነው። ፀጥ ያለው መኝታ ክፍሉ ከፍ ያለ የትንፋሽ መቆራረጥ ድምፅ ማስደመጥ ጀምሯል። አሁን ደግሞ እንደጩኸት ያለ የስሜት ሲቃ ይሰማል። ኢስማኢል በሚቆራረጥ ድምፅ "እወ ድሻ ለ ሁ፣ እ ወድ ሻ ለሁ" እያለ ከእግሮቿ መካከል ወደ ፊት ወደ ኋላ ይመላለሳል። የሀያት ጩኸት እያየለ ነው። ከአልጋው በስተጀርባዋ ተዘርራ የክፍሉን ጣሪያ እያየች እጆቿን ለመታገል በሚመስል አይነት ከእጆቹ ጋር ታፋትጋለች። ያመልጣት ይመስል እግሮቿን አጠላልፋቸዋለች። ብዙ ጩኸት ፣ ብዙ ሲቃ ፣ ብዙ "እ ወድ ሻለ ሁ" ተደመጠ። ነጩ አልጋልብስ በተቀላ ክብር ደም በሰበሰ። ክብሯ ከኢስማኢል ጭን መሀል ተሰዋ። ድንግልናዋን ፣ እሷነቷን ካወቀችው ገና ሳምንት እንኳ በቅጡ ላልሞላው ለኢስማኢል አስረከበችው። የስሜት ትንቅንቁ ሲያባራ ተፋፈሩ። ኢስማኢል በጣም ደንግጧል። በፍፁም ድንግል አልመሰለችውም ነበር። ዝም እንደተባባሉ ፣ እንደተፋፈሩ ተያይዘው ከሆቴሉ ወጡ። መኪናዋ ከሱሉልታ እስከ አዲስአበባዋ ተክለሀይማኖት ድረስ ስትዘልቅ ምንም አልተነጋገሩም። ምንም። የመኪናው ቴፕ ሁለቱም የሚወዱትን የጥላሁንን "ፍቅርሽ ነው የጎዳኝ" የሚለውን ሙዚቃ ታንቆረቁራለች። እንደተፋፈሩ ፣ ዝም እንደተባባሉ ተክለሀይማኖት ደረሱ። ቻው ሳትለው ከመኪናው ወረደች። ከራሷ ጋር ትልቅ ጭቅጭቅ ውስጥ ገብታለች። "እንዴት ሳምንት ለማውቀው ሰው ክብሬን ሰዋሁት?" "አባባ ቢሰማ ምን ይል ይሆን?" እያለች መልሳቸው ግራ የሚያጋቧትን ጥያቄዎች ራሷን ትጠይቃለች።

.
ቤት እንደገባች ከማንም ጋር ሳትነጋገር ወደ መኝታ ክፍሏ ገብታ በሩን ቆለፈችው። ልቧ መረጋጋት ተስኖታል። በጣም ፈርታለች። ኢስማኢል ደወለ ፣ አይታ ተወችው። እየደጋገመ ይደውላል ፣ አታነሳም። መደጋገሙ ሲበረታ ስልኩን አነሳችው። ኢስማኢል የቅድሙ ፍርሀቱ ሳይለቀው በለዘቡ ቃላት ያወራታል።
"የኔ ቆንጆ ፣ መቼም አልተውሽም እሺ ፣ መቼም"
"እሺ"
"ከማንም በላይ እወድሻለሁ እሺ ፣ የኔ ፍቅር"
"እሺ"
እሺ ከማለት በዘለለ ምንም አታወራም። የሆነው ነገር ሁሉ ግራ አጋብቷታል። ወንዳወንድነቱን የምታመልከለት ኢስማኢል እግሮቿ መሀከል ወደ ፊት እና ወደ ኋላ እየተመላለሰ ሲያላዝን ቅፍፍ ብሏታል። እንደዛ በእርጋታ የምታወራው እሷ ፣ በጀርባዋ ተንጋላ የሚደብር አይነት ጩኸት ስትጮህ ለራሷም ቀፏታል። በዚሁ ስሜት ውስጥ እንዳለች የአልጋው ኮመዲኖ ላይ የተቀመጠውን ማስታወሻ ደብተር አንስታ ባለ ሁለት ስንኝ ግጥም ሞነጨረች። ዜማውን ለመገምገም ጮክ ብላ አነበበችው።

"የምትሞቺለትን ፣ ዛሬ ቀመስኩት፣
ከፊሉ ደስታ ነው ፣ አብላጫው ውርደት።"
የተሰማትን ስሜት ከወረቀት ጋር አዋደደችው። ይህን የዛሬውን ታሪኳን ማንም ባይሰማ ደስ ይላታል። የመኝታ ክፍሏ በር ተሞነጨረ። ታናሽ እህቷ ገና ለወሬ ባልጠናው አንደበቷ "አዩ ፣ አዩ" እያለች ከተዘጋው የመኝታ ቤቷ በር ጋ ትታገላለች። ሀያት ከአልጋዋ ተነስታ በሩን ከፈተችና ከመሬቱ ላይ አንስታ አቅፋት ወደ ውስጥ አስገባቻት። አልጋው ላይ አስቀምጣ ጣቶቿን እያማታች ለማጫወት ሞከረች። አባቷ ወደ ክፍሏ መጡ። ሀያት በጣም ደነገጠች። "እዚህ ተቀምጠሽ ነው እንዴ የምትፈለጊው? በይ ልጅቷ ሳትሸና አልቀረችም ፓምፐርሱን ቀይሪላት። ደሞ ልጅቷ የት ሄደች?"
"አሁን ወጣች ፣ የት እንደሄደች አላወቅኩም።"
ሀያት በድንጋጤ ሆና መለሰች እንጂ ሰራተኛቸው ወደ ቤት ስትገባም አልነበረችም። አባቷ ፊቷን አይቶ የዋለችበትን ሁኔታ የሚረዳ መስሏት ተቁነጠነጠች። አባቷ ግን ወዲያው ወደ ሳሎን ተመለሱ።
.
የተፈጠረውን ነገር ለማን መተንፈስ እንደምትችል ታውጠነጥናለች። ለቤቲ ልትነግራት ስልኳን አነሳችና ቅፍፍ ሲላት መልሳ አስቀመጠችው። ስለ ኢስማኢል አሰበች። የሷ እንደሆነ ስታስብ በጣም ደስ አላት። ወደ ፌስቡክ አካውንቷ ገባችና የፌስቡክ ስሟ በቅንፍ ውስጥ "እስሚዝ ህይወቴ" የሚል ፅሁፍ እንዲጨምር አደረገች። ፕሮፋይል ፒክቸሯን በኢስማኢል ፎቶ ቀየረችው። ማንም ምንም ቢል ግድ አይሰጣትም። ቤተሰቦቿ ከማህበራዊ ሚዲያ የራቁ ስለሆኑ አይመለከቱትም። ውዷ መሆኑን አወጀች። ፈገግታው እየናፈቃት ፣ ሁሌም የሷ ብቻ እንዲሆን ተመኘች።
.
ሀያት ከገባችበት የመፍዘዝ አለም ካገገመች በኋላ ኢስማኢልን ደውላ አወራችው። ኢስማኢል በጣም ደንግጦ ስለነበር እየደጋገመ ላይለያት ይምላል።
በነጋታው ቁርስ ይዞላት ወደ ሰፈራቸው መጣ። ቁርስ እሱ መኪና ውስጥ አብረው በሉ። አዲስ የተጋቡ ጥንዶች ይመስላሉ። ሲጎራረሱ ፣ ሲጎሻሸሙ ፣ አይን ለአይን በፍቅር ሲተያዩ ፍቅራቸውን ቤተሰብ ተቀብሎ ያወጀው ይመስላል። ግን አይደለም። የማህበረሰቡ እሴት በሚፈልገው መልኩ በጋብቻ አልተሳሰሩም።
.
ጊዜው እየገፋ ሀዩ እና ኢስማኢል ከተዋወቁ ሶስተኛ ሳምንታቸው ደረሰ። በዚህ መካከል የሱሉልታውን ትንቅንቅ አንዴ ሀዋሳ ሀይሌ ሪዞርት ውስጥ ደግመውታል። ዛሬ ሀዩ ለየት ያለ ስሜት ተሰምቷታል። እንደማቅለሽለሽ ያለ ስሜት ሲፈታተናት ከትምህርት ቤት ቀርታ ወደ ክሊኒክ ሄደች። ለሀኪሟ ስሜቷን ካስረዳቻት በኋላ ምርመራ ተደረገላት። ሀያት በነዛ ትንቅንቆች ምክንያት አርግዛ ነበር። ማመን በጣም ከበዳት። በዘርፉ ብዙም ልምድ ስለሌላት የወሊድ መቆጣጠሪያ መንገዶችን በአግባቡ አልተጠቀመችም ነበር። በጣም ፈርታለች። የተረገዘው ህፃን ገና ከሶስት ሳምንት አልዘለለም። ሀዩ ምን ማድረግ እንዳለባት በጣም ግራ ገብቷታል። ለኢስማኢል ደወለችለት።
"ወዬ ፍቅር"
"ውዴ ዛሬ ክሊኒክ ሄጄ ነበር"

"ምነው ቆንጂት አመመሽ እንዴ?"

"እንደዛ ነገር ነበር ግን ስመረመር"

"ስትመረመሪ ምን?"

"ስመረመርማ አርግዘሻል ተባልኩ"

ኢስማኢል በጣም ደነገጠ። በጣም። ከሰዓት በኋላ ለመገናኘት ተቀጣጠሩ። እናቷ ልጃቸው ከትምህርት መቅረቷ በጣም አሳስቧቸዋል። አመመኝ ስላለች የምትወደውን ምግብ ሰርተው ደስ ሊያሰኟት እየሞከሩ ነው። በመሀል ወደ መኝታ ቤቷ መጥተው ክሊኒክ ምን እንዳሏት ጠየቋት።

"ምን አሉሽ ሀዩዬ? መድሀኒት አዘዙ?"

"መድሀኒት አልሰጡኝም። ማስታገሻ ብለው መርፌ ወጉኝ።"

"በሽታው እንዲህ ነው ብለው አልነገሩሽም?"

"የጨጓራሽ ስሜት ነው ነው የሚሉት"

ሀያት ጨጓራዋን ሌላ ጊዜም ያማት ስለነበር ቆንጆ ማሳበቢያ ሆኗታል። መርፌ የሚባል አልተወጋችም። ግን መዋሸት ነበረባት። የተፈጠረውን እናቷ ቢያውቁ ሰው አይሆኑም። አባቷ ቢያውቁ ደግሞ እሳቸውም እሷም በህይወት አይኖሩም።

.

ከከሰዓት በኋላ ከኢስማኢል ጋር ተገናኙ። ሀዩ በጣም ፈርታለች። ከመኪናው ቴፕ ዛሬም "ፍቅርሽ ነው የጎዳኝ" የሚለው የጥላሁን ሙዚቃ ይንቆረቆራል። መኪናውን ወደ ዶዲ ነዳው። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ተገናኙበት ቦታ! ዶዲ ሲደርሱ በአውራጣቱ የቅንድቧን ፀጉር እያሻሸ አይኖቿ ውስጥ ቀልጦ ማውራት ጀመረ።

"ሀዩ ምንድነው የሚሻለን?"

ሀያት ዝም ብላ ታየዋለች። አብረው መኖር አይጀምሩ ነገር ገና ከአባቱ ድጋፍ ነፃ ሆኖ በራሱ አልቆመም። ግራ ግብት ብሎት ሲፈዝ እሷ መናገር ጀመረች።

"ኢስማኢል በቃ ላስወርደው!"

"ምን?"

"በቃ ላስወርደው ታዲያ ምን አማራጭ አለን?"

"ማስወረድማ በፍፁም አይታሰብም!"

"ማርገዜ ተሰምቶ ቤተሰቦቼ ከሚዋረዱ ሞቴን እመርጣለሁ። በፍፁም እንደዚህ ያለ ውርደት ውስጥ መግባት አልፈልግም።"

"ልጁን ማስወረድማ ..."

ቃላቱ ምክንያታዊነት አጡበት። ልጁ ይወለድ ከተባለ ለሀያት እና ለቤተሰቦቿ ትልቅ ቅሌት ነው። ሳይፈልግ በሀሳቧ ተስማማ። በነጋታው በአዲስ አበባ ውስጥ የተረገዙ ህፃናትን በመግደል ታዋቂ ወደ ሆነ ሰማያዊ በነጭ ክሊኒክ ሄዱ። ዛሬ ያሉበትን ቦታ ሁለቱም እንቆምበታለን ብለው አስበው አያውቁም። ከሰዓታት በኋላ ህፃኑ ማህፀኗ ውስጥ በብረት እየተቆራረጠ እንዲወጣ ተደረገላት። አንድ ምንም ያላጠፋ ህፃን ፣ አንድም ሰውን ያልበደለ ታዳጊ ፤ ገና ወደ ምድር ሳይመጣ ከምድር ክፋት ያዘለ

ብረት ወደ ተሸሸገሸት አለም ሾልኮ ሄዶ ቆራረጠው። አንድ የተከበረ ከሀጢአት የፀዳ ሰው ሞተ።

.

ከክሊኒኩ ወጥተው ወደ ቤታ ሊያደርሳት መንገድ ጀመሩ። መኪናው የተበላሸ አስፓልት ጋር ደርሳ ገጭ ባለች ቁጥር ሀያት የሚያሳዝን የስቃይ ድምፅ ታሰማለች። መኪናው ገጭ ባለ ቁጥር ኢስማኢል ነብሱ ከስጋው ልትነጠል ትደርሳለች። እጆቿን ጭምቅ ያደርጋታል። አንዴ መኪናው ገጭ ሲል ሀያት በጣም አመማት ፣ የሚያሳዝን የስቃይ ድምፅ አሰማች። ኢስማኢል ከአይኑ እንባ ወረደ። ህመሟ አመመው። ወንድነቱ ተረታ፤ አለቀሰ።

.

ሀያት ሲቆይ ህመሙ እየቀነሰ ፣ እየቀነሰ ሄዶ ተሻላት። ልጇን እንዳስወረደች ስታስብ በጣም ትፀፀታለች። ኢስማኢል ሲያደርግላት የነበረው እንክብካቤ አቅሏን ነስቷታል። በጣም አሳዝኗታል። ሲያለቅስ የነበረውን ስሜት እያስታወሰች ፈገግ ትላለች። ኢስማኢልን እያሰበች አንድ ግጥም ሞነጨረች። ሁሌም እንደምታደርገው ለራሷ በሚሰማ ድምፅ አነበበችው።

"ይሁን ያልከው ሆኗል ፣ እሰዋለሁ ላንተ፣

ምንም እችላለሁ ፣ አንተን ካስደሰተ።

ተዪኝ ግን እንዳትል ፣ እንዴት እችላለሁ?

አሊያም ደስ እንዲልህ ፣ ኑሬ አልችልምና እሞትልሀለሁ።"

.

ሀያት እና ኢስማኢል የአፍላ እድሜ ፍቅቅሮሻቸውን ቀጠሉ። የሳምንቱ የመጨረሻውን ቀናት ማለትም ቅዳሜን አሊያም እሁድን ከከተማ ወጣ ይላሉ። አንዳንዴ እነዚያ ትንቅንቆች ይደገማሉ። ኢስማኢል የሚይዘው ብር ሲታይ ገና ሀያ ሶስት አመት ያልሞላው አይመስልም። የሷም ሰውነት ሲታይ ገና አስራ ስምንት አመት አልሞላትም ቢባል ማንም አያምንም። በጣም ትልቅ ይመስላሉ። ስለምንም ስለማንም ማሰብ አይፈልጉም። እነሱ ብቻ ፣ አዎ እነሱ ብቻ የምድር ጌጦች ናቸው። ለነሱ

.

ሀያት እና ኢስማኢል ከተገናኙ ሶስት ወራት ተቆጠሩ። ሀያት ከሱ ጋር ያሳለፈቻቸውን ጊዜያት በቅደም ተከተል ተናገሪ ብትባል ያለአንዳች መዛነፍ መተረክ የሚያስችል ቆንጆ የትዝታ መዝገብ አላት። እሱን ስታስብ ሁሌም ደስታ ትዝ ይላታል። ዛሬ በጠዋቱ ደወለችለት። የሳምንቱ የእረፍት ቀን ስለሆነ ዛሬም እንደሁሌው እንገናኛለን በሚል ተስፋ! ኢስማኢል ግን ዛሬ በፍፁም እንደማይመቸው ነገራት። በስራ ተወጥሯል በሚል ሀሳብ መልካም ቀን ተመኝታለት ስልኩን ዘጋችው። ማታውን ይደውላል ብላ ብትጠብቅም አልደወለም።

ሀያት ታናሽ እህቷን ስታጫውት ፣ ከእናቷ ጋር ማዕድቤት ጉድ ጉድ ስትል ነበር የዋለችው። አባቷ ወደ ቤት ሲገቡ ሳሎን ላይ የወደቀ አንድ ወረቀት አግኝተው ማንበብ ጀመሩ። የፈተና ወረቀት ነበር። ሀያት ህፃኗን ለማባበል አስይዛት የነበረ ነው። አምስት ከሀያ ያገኘችበት ፈተና ነበር። አባቷ በጣም ደነገጡ። ተቆጡ። ፈተናዋን ስራዬ ብለው አይተው ባያውቁም ዛሬ በድንገት ባዩት ውጤት ተበሳጩ። ከልጃቸው እንደዚህ ያለ ውጤት ጠብቀው አያውቁም ነበር።

.

ቤቲ እና ኤርሚያስ ያሳለፏቸውን የመመቻቸት ጊዜዎች ጨርሰው ላሽ ተባብለዋል። ቤቲ ሄኖክ የሚባል ተረኛ ፍቅረኛ ይዛለች። ትንሽ የተረጋጋ ማንነት የላትም። ኤርሚያስም አዲስ ሴት ጠብሷል። ሁሉም ነገር በቤቲ እና በኤርሚያስ ህይወት ውስጥ እቃቃ ነው። ዛሬ ተጀምሮ ነገ ይፈርሳል። ጊዜያዊ ጥምን ማርካት የሁለቱም የህይወት መስመር ነው። በእነርሱ ህይወት ውስጥ ሀይማኖት ፣ ባህል ፣ ስነ ምግባር የሚባሉ ነገሮች ብዙም ቦታ የላቸውም።

.

ቀናት እየገፉ ሄዱ። ኢስማኢል እንደ ድሮው ከሀያት ጋር አይገናኝም። እያለ እያለ ደግሞ ስልክ መደወልም አቆመ። ሀያት በጣም ተረብሻለች። ውዷን ምን እንደነካባት ግራ ገብቷታል። ስትደውል ያወራታል ፣ ወሬው ግን እንደሌላ ጊዜው ብዙም ጣዕም የለውም። ቀናት እየገፉ ሲመጡ ስልክ ስትደውልለት አለማንሳት ጀመረ። ትናንት አብረው ብዙ ነገሮችን አድርገዋል። ከሁሉም የሚከብደው ክብሯን አሳልፋ ሰጥታዋለች። በእርሱ ምክንያት ምንም የማያውቅ ህፃን አስወርዳለች። ሀያት ሁሉ ነገር ጨለመባት። እንባዋ ታረቃት። ሁሌ ማልቀስ ስራዋ ሆነ። ኢስማኢል ከድቶኛል ብላ ለማሰብ አትፈልግም። አንዳንዴ ብቻዋን ክፍሏ ውስጥ ትቆምና ከስልኳ ስክሪን ላይ ፎቶውን እያየች "ምን ነካብኝ የኔ ንጉስ? ምን ነካብኝ?" እያለች ተንሰቅስቃ ታለቅሳለች። የተፈጠረውን ነገር ለሳሚያ እና ቤቲ ነገረቻቸው። እነርሱ ግን ኮራ እንድትልበት ከመምከር በዘለለ ምንም ሊፈይዱላት አልቻሉም። ልቧ ሊቆርጥለት አልቻለም። ኢስማኢል መጥፎ ሰው አይደለም ብላ ትሞግታለች። ዛሬም ትንሰፈሰፍለታለች።

.

አንድ ቅዳሜ ጠዋቱን ሀያት ታናሽ እህቷን ሱመያን አልጋዋ ላይ አስቀምጣት በሩን ቆለፈችው። ህፃኗ ገና ንግግር የመረዳት ደረጃ ላይ አልደረሰችም። ሀያት እየተንሰቀሰቀች ከኢስማኢል ጋር ያሳለፈችውን ጊዜ ለህፃኗ ተረከችላት።

"ሱሚ እድግ ስትዪ ወንዶች እወድሻለሁ ቢሉሽ አትመኚቸው እሺ!" እንባዋ ሳጓን ያጠነክረውና ከመናገር ይገታታል። ራሷን ለመቆጣጠር ትሞክርና ንግግሯን ትቀጥላለች።

"ሱሚ እነሱ የስሜት ጥማቸውን ሊያረኩብሽ ፣ ሊለማመዱብሽ ነው እሺ መቼም እወድሻለሁ ሲሉሽ አትመኚ! ይኸው እኔን እንኳ ክብሬን የሰጠሁት ኢስማኢል ፍቅርሽ ነው የጎዳኝ ሲለኝ እንዳልነበር ዛሬ ለሽታ እንኳ ራቀኝ።"

ህመሙ ቢወጣልኝ ብላ ንግግሯን ለማትረዳት ህፃን ትዘረግፈዋለች። ለቅሶዋ እጅጉን በረታ እየተንሰቀሰቀች " ሱሚ እድግ ስትዪ ካላገባሽው ወንድ ጋር እንዳትሳሳሚ እሺ ፣ ከተሳሳምሽ አብረን እንተኛ ይልሻል ፣ አብረሽው ከተኛሽ ደግሞ ክብርሽን ታጪያለሽ ፣ ክብርሽን ካጣሽ ደግሞ ይንቅሻል። ወንድ አትውደጂ እሺ ሱሚዬ" ለቅሶዋ እየጠና ሲመጣ ሱሚ አብራት እየጮኸች ማልቀስ ጀመረች። ሀያት ፊቷ በእንባ ታጥቧል። ሱሚን አባበለቻትና መሀል ጣቷን ከአውራ ጣቷ እያማታች ልታጫውታት ሞከረች።

.

ሀያት ስታኮርፍ ኢስማኢል አንገቷ ስር ይነክሳት ነበር። አንዳንዴ ደግሞ ሳቂ ይላትና ስትስቅ ጥርሷን ይስማት ነበር። ዛሬ እነዛ ሁሉ ፍቅር ይመስሉ የነበሩ ቀናት እንደጠወለገ አበባ ውበታቸውን

ተነጥቀዋል። ስልኳን አንስታ ሰሞኑን የጀመረችውን አንድ ልብወለድ ቴሌግራም ላይ ማንበብ ጀመረች። አርዕስቱ "የማይፋቅ ስህተት" ይላል። በምታነበው ታሪክ ውስጥ ያለችው ፌቨን የምትባለው ገፀ ባህሪ የደረሰባትን ህመም ከራሷ ህመም ጋር አመሳሰለችው። ፀሀፊውን ብታናግረው ደስ አላት። ከልብወለዱ አርዕስት ስር ያለውን ስሜን ፌስቡክ ላይ አስሳ አካውንቴን አገኘችው። መልዕክት ስታስቀምጥልኝ ፌስቡክ ላይ ብዙም ስለማልቆይ በቴሌግራም እንድታወራኝ ዩዘርኔሜን ላኩላት። ሁሉንም ታሪኳን አጫወተችኝ። ከእኔ ጋር የተዋወቅንበት ቅፅበት ይኸው ነው። ሁሌም የተሰማትን ትልክልኛለች እኔም በቻልኩት አማክራታለሁ።

.

ቀናት ከሄዱ በኋላ እሁድ ማታውን ኢስማኢል ደወለላት። የሚናገረው ተመሳሳይ ነገር ነው። "ጊዜ እፈልጋለሁ ፣ ራሴን ልወቅ" ነበር ቃሉ። ራሱን ከማወቁ በፊት ነበር የተኛት ማለት ነው? ቀናት ሲሄዱ ኢስማኢል የሀያት ጓደኛ እንደሆኑ የማያውቃቸው ጓደኞቿ ፎቶ ስር ኮመንት መስጠት አበዛ። አሁንም የሀያት ምኞት ልቡ አደብ ገዝቶ የድሮው ኢስማኢል ቢሆንላት ነው። የፈጣሪዋን ትዕዛዝ መጋፋቷን ራሷም አትዘነጋውም። ታሪኳን በፃፈችልኝ ቁጥር ጌታችን እንዲምረን ዱዓ አድርግልን ትላለች። ከሁሉም የገረመኝ ደግሞ ምህረቱን ለእሷ ብቻ ሳይሆን ለእርሱም መመኘቷ ነበር። ዛሬም ትወደዋለች። ዛሬም ታፈቅረዋለች።

.

የተወለደችበት ጥር ሀያ ስድስት ቀን ሲደርስ እኔ ቤት መኝታ ክፍል ውስጥ ተኝቼ በስልኬ ማስታወሻ ላይ የዚህን ፅሁፍ ክፍል አንድን እየፃፍኩ ነበር። ታሪኳን ለማስታወስ የላኩችልኝን ድምጾች ሳደምጥ "አስራ ስምንት አመቴን ጥር ሀያ ስድስት ነው የምይዘው" ያለችበትን ሰማሁና ሊሰማት የሚችለውን ህመም እያሰብኩ "ዛሬ 18+ ሆንሽ አይደል?" የሚል መልዕክት ላኩላት። ዛሬ የተወለደችበት ቀን እንደሆነ ማሰብ እንዳልፈለገች በሚያሳብቅ ሁኔታ "አዎ" ብቻ ብላ መለሰችልኝ። ምናልባትም እያለቀሰች ይሆናል።
ወደ ማታ ላይ ኢስማኢል ደውሎላት "ሀፒ በርዝደይ" እንዳላት ነገረችኝ። እንደድሮው ቢሆን በሚገርም ትዕይንት ሊያከብሩት ይችሉ ይሆናል። ግን የነበሩበት የፍቅር ግንኙነት ምንም አይነት ህጋዊ ድጋፍ ስለሌለው እንደእቃቃ ሆ ተብሎ ተመስርቶ ሆ ተብሎ ፈረሰ።

.

ዛሬም ብዙ ሰዎች ታሪኳን ሲሰሙ "ይህቺ ሴት ናት እንዴ? ደሞ ራሷ ስማው!" "ቲሽ እንዴት አብራው ትተኛለች? ባለጌ!" እያሉ ሊወቅሷት ይሞክራሉ። አዎን ትናንትም እሷ እንደዚህ ያሉ ተመሳሳይ ታሪኮችን ብትሰማ ልትል የምትችለው ይኼን ሊሆን ይችላል። ግን ዛሬም ብዙ አፍላ ወጣቶች ከሚወዷቸው ቤተሰቦቻቸው ፣ ከሚሳሱላቸው ወላጆቻቸው ፊት የእሳቱ እድሜ ወላፈን ዞር ሲያደርጋቸው ያደጉ እየመሰላቸው አንሶላ መጋፈፍ ጀምረዋል። ሊያስከፍለው የሚችለውን ዋጋ ግን ለማሰብ አልቻሉም።

.

በሰዓቱ ታሪኳን ስታጫውተኝ በፈተና የተጨናነቅኩበት ጊዜ ስለነበር ወዲያው ልፅፈው አልቻልኩም ነበር። ስለ ታሪኳ ሳስብ ሁሉንም እውነት ፣ ሁሉንም እሳት ያለምንም ሸሸግ ልፅፈው ለራሴ ቃል ገባሁ።

ሁሉንም እውነት ፣ የመኝታ ክፍሉን ትንቅንቅ ሳይቀር በግልፅ አማርኛ ፅፌዋለሁ። ይህ ማስተዋል ለሚችሉ ወጣቶች ሁሉንም የህይወት ጎን ተመልክተው የነገሩን መልካምነት አሊያም ጎጂነት በራሳቸው እንዲወስኑ ነፃ የማመዛዘን እድል ለመስጠት በማሰብ ያደረግኩት ነው። ታሪኩ ላይ ጥበባዊ ይዘት ከመጨመር በዘለለ ከዋናው ታሪክ ጋር የሚቃረን ምንም አይነት ታሪክ አልጨመርኩም። በታሪኩ ላይ የተጠቀሱት ስሞች የግለሰቦቹን ማንነት ለመደበቅ ሲባል የተቀየሩ ናቸው።

.

ሀያት ዛሬ ያጣችውን ድንግልናዋን እና ያስወረደችውን ንፁህ ህፃን ስታስብ የኢስማኢልን መጨረሻ ያሳየኝ ትላለች። ከመኝታ ክፍሏ ተቀመጠችና ማስታወሻዋን አንስታ ግጥም ሞነጨረች።

"ጨለማ ነበረ ፣ ብርሀን ነበረ፣
ውብ እንባም ነበረ ፣ ፈገግታም ነበረ፣
ከመንከትከት መሀል ፣ ሰርጾ የተቀበረ፣
አይታይም እንጂ
ጥርሶች የሸፈኑት፣ በድፍረቱ ያፈረ፣
በበደል ተበጥቶ ፣ ቁስሉ ያልሻረ፣
ክብሩን የተቀማ ፣ ሴትነት ነበረ።
ነበር ተሰበረ ፣ እንባ ታየ ገኖ፣
የፈገግታ ሽፋን ፣ መረታቱን አምኖ፣
ከዛም ብዙ ለቅሶ ፣ ከዚያም ብዙ ዋይታ፣
የፈሰሰ ውሀ ፣የሚያፍስ ሰው አጥታ።
ወየው ማለት ብቻ ወዮልኝ ለራሴ፣
የኔው አንዲት ትንፋሽ ስትጠፋ ሞገሴ።
ወየው ብቻ ቃሉ፣
ወየው ብቻ ለኔ፣
ምን ያብሰው ይሆን ይህንን ኩነኔ?
ወየው ብቻ ለኛ!!!!!"

ከዚያም አለቀሰች። ብሶት በሞላው ድምፅ ከኢስማኢል ጋር አብረው ያንጎራጉሩት የነበረውን ሙዚቃ በወንድ ቀይራ ጮክ ብላ መዝፈን ጀመረች።

"ፍቅርህ ነው የጎዳኝ ፣ ፍቅርህ ነው የጎዳኝ ፣ ፍቅርህ ነው የጎዳኝ!
በልቼ እንዳልበላሁ ፣ ጠጥቼ እንዳልጠጣሁ ፣
ያረገኝ ፍቅርህ ነው ፣ መች አጣሁ መች አጣሁ።
ከሰው ተራ አውጥቶ ያረገኝ ብቸኛ ፣ አውቃለሁ ፍቅርህ ነው ፣ ይሄ መዘዘኛ ፣ ይሄ መዘዘኛ።
ነጭናጫ ያረገኝ ፣ ተቆጪ በቶሎ፣
ያው ያንተው ፍቅር ነው ፣ ሌላ ማን ተብሎ ፣ሌላ ማን ተብሎ?"

ዛሬ እንደትናንቱ እየሳቀች አይደለም የዘፈነችው። ከአጠገቧ አብሯት የሚጮህ ወንድ አልነበረም። ለፍቅቅሮሽ ማጀቢያም አልነበረም። ግን የእውነት ተጎድታ የእውነት እንባዋ እየፈሰሰ ፣ የእውነት ክብሯን እየናፈቀች ይመለስ ይመስል ፤ ታለቅሳለች ያ ሁሉ አልለይሽም የት እንደገባ ግራ ገብቷታል።

ታለቅሳለች ለቅሶ መፍትሔ ይመስል።
በጠዋቱ ቴሌግራም ላይ የማወራው ሰው ስለነበር ቤት ውስጥ ኮኔክሽን ስላስቸገረኝ የቤታችን የውጪ በር ላይ ቆሜያለሁ። በመሀል የሀያት መልዕክት ገባልኝ።
"ፉፉ"
"እ ሀዩ"
"የሚያስቅ እብደት ውስጥ ነኝ"
"ምነው?"
"ኢስማኢል እኮ ፕሮፋይሉን በሌላ ሴት ፎቶ ቀየረ። ፍቅሬ ናት ምናምን ብሎ"
በጣም ስላሳዘነችኝ ሌላ ምንም ልላት አልቻልኩም።
"አዝናለሁ ሀዩ አይዞን!" ከማለት ውጪ።
.
ተፈፀመ!!